Department of Community and Human Services

alexandria community services board

4850 Mark Center Dr. • Alexandria, VA 22311 • 703.746.3400 • alexandriava.gov/CSB

# የጤና መዝገብዎ አያያዝ ምስጢራዊነት

## የጤና መዝገብዎ ውስጥ ስላለው መረጃ አጠባበቅ እና ምስጢራዊነት

መዝገቦችዎ በጥብቅ በሚስጢር ይያዛሉ። ይህም በኮምፒተር ሲስተም ውስጥ የተከማቸውን የጽሑፍ መረጃ፣ የቃል ንግግሮች እና ኤሌክትሮኒክ መረጃዎችን ያካትታል። ሁሉም መዛግብቶች ደህንነታቸው ተጠብቀዋል። በሕክምናዎ ውስጥ የተሳተፉ የ CSB ሠራተኞች ብቻ የእርስዎን መዛግብቶች ያለ እርስዎ ፈቃድ ማየት ይችላሉ። ከሚከተሉት ሁኔታዎች በአንዱ ካልሆነ በስተቀር፣ የእርስዎ መዛግብት ወይም ስለ እርስዎ ያለ መረጃ ለሌሎች የሚለቀቁት በእርስዎ የጽሑፍ ፈቃድ ብቻ ነው፡

- ድንገተኛ ክስተቶች፤ በራስዎ ወይም በሌሎች ላይ ሞትን ወይም ጉዳትን ለመከላከል፣ ወይም የየንብረት ውድመትን ለመከላከል ሲባል ስለእርስዎ መረጃ ልንሰጥ እንችላለን።
- ሠራተኞች፤ ለእርስዎ አገልግሎት ለመስጠት ወይም የተቀበሏቸውን አገልግሎቶች ለመከታተል ማወቅ ለሚፈልጉ ሌሎች የ CSB ሠራተኞች ወይም በአግባብ ለሰለጠኑ ፈቃደኛ ሠራተኞች መረጃ ልንሰጥ እንችላለን።
- ክፍያ፡ ለአገልግሎቶች ክፍያ ለመሰብሰብ አስፈላጊ የሆነውን መረጃ ለኢንሹራንስ ኩባንያዎች ወይም ለሌሎች ሶስተኛ ወገንዎች ልንሰጥ እንችላለን።
- የህግ መስፈርቶች፤ ፍርድ ቤት እንድንሰጥ ካዘዘ፣ ወይም ከሌሎች የስቴቱ ወይም የፌዴራል ህጎችን ለማክበር በሚፈቅደው መጠን መረጃዎን ከመረጃ መዝገብዎ ልንሰጥ እንችላለን። እንዲሁም በጉዳይ ላይ የኛ የሕግ አማካሪ ሲወክለን መረጃን ልንሰጥ እንችላለን። ህክምናው በሕግ ሂደት ውስጥ የታዘዘ ከሆነ፣ በፍትህ ስርዓት ውስጥ የጤና መረጃውን ለመከታተል መረጃውን ለሚፈልጉ ግለሰቦች መረጃ ልንሰጥ እንችላለን።
- ጥበቃ፤ እርስዎ በሌል ግለሰብ ላይ የሕይወት ወይም የአካል ጉዳት የሚያደርሱ መሆንው ከታመነ ስጋቱን ለማስቀረት እና የሌሎችን ዱንነት ለመከላከል አስፈላጊውን መረጃ ብቻ ልናጋራው እንችል ይሆናል።
- የኤች አይ ቪ ስጋት፤ በ CSB ምርመራ ኤች አይ ቪ/ኤድስ፣ ሳንባ ነቀርሳ ወይም ጉበት ከተገኘብዎት ይህንን መረጃ ለጤና ክፍል ማሳወቅ አለብን።
- ጥቃትና ወይም ቸልተኝነት፤ የተጠረጠረ ጥቃትን ወይም ቸልተኝነትን ለሚመለከተው እአካል ለማሳወቅ እኛ ስለእርስዎ መረጃ ልንሰጥ እንችላለን።
- ወንጀል፤ በ CSB ግቢ ሆነው በንብረት ወይንም በ CSB ሰራተኞች ላይ ወንጀል ቢፈፅሙ እና ወንጀል ለመፈጸም የሚያስፈራሩ ከሆነ፣ መረጃን ለባለሥልጣኖች ሪፖርት ይደረጋል።
- ሰብዓዊ መብቶች፡ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን ለመመርመር እአስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በአካባቢያዊ ለሚግኝ የሰብአዊ መብት መርማሪ እአካል አስፈላጊ የሆነውን ማንኛውንም መረጃ ልንሰጥ እንችላለን።
- ምርምር፤ ለምርምር ዓላማ ወይም የህዝብ ቆጠራን ለማስላት ሲባል ስለእርስዎ ያለንን እአስፈላጊ መረጃ ልናሳውቅ እንችላለን። ይህ መረጃ ኝ ስምዎን ሆነ ማንነትዎን አያጋልጥም።
- አስተዳደር፤ ለፍቃድ ሰጪ እአካል፣ ኩነት ማረጋገጫ፣ ለአስተዳደር እአካል፣ ለፋይናንስ ኦዲት እንዲሁም ለፕሮግራም ግምገማዎች ዓላማ መረጃ ልንሰጥ እንችላለን።

## ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን መዝገቦች እአጠቃቀምና ይፋ ለማድረግ ፈቃድ ስለመስጠት

ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች ከወላጅ ወይም አሳዳጊ ፍቃድ ሳያገኙ አገልግሎቶችን ስለመቀበል፤ በአብዛኛዎቹ ሁኔታዎች፣ አንድ ልጅ ወላጅ ወይም አሳዳጊው ሳያውቅበ CSB ውስጥ አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚፈልግ ከሆነ፣ እሱ/እሷ ለሕክምናው ዉሳኔ ውስጥ ወላጆቹን ወይም አሳዳጊዎቹን እንዲያካትት ይጠየቃል/ትጠየቃለች። ልጆች ማንንም ያለማካተት መብት አላቸው፣ ይህ በሚሆንበት ሁኔታ CSB ወላጅ ወይም አሳዳጊ ጋር መገናኘት ወይንም መረጃ ማጋራት እአይቻልም ይሆናል። ልጁ ካለወላጅ/እአሳዳጊ ህክምና ለማግኘት በህግ በተሰጠው መብት መሰረት ከተስማማ፣ ወላጅ ወይነም አሳዳጊ በሚመመለከተው እአካለ በልጁ ላይ ወይንም በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል ብሎ ካልተወሰነ በስተቀር ወላጁ/እአሳዳጊው የልጁን የአእምሮ ጤና መዝገብ እንዲያገኝ ይፈቀድለታል። ወላጁ/እአሳዳኢ የልጁን የአደንዛዥ ዕጾችን አላግባብ መጠቀም መዝገብ እንዲያገኝ ወይም እንዲያነብ አይፈቀድለትም። ነገር ግን ለአካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ግን የእጽ መጠቀምን የሚያሳይ መዝገብም ሆነ የአእምሮ ጤና መዛግብትን ይፋ እንዲወጡ ሊስማማ ይችላል። ወላጅ/እአሳዳጊ በግላ ይፋ ማድረግ ግን አይችልም

ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች ወላጅ ወይም አሳዳጊቀ አገልግሎቶችን መቀበል፤ አንድ ልጅ በወላጅ ዕውቀት እና ስምምነት የአእምሮ ጤና አገልግሎቶችን ከተቀበለ፣ ወላጁ እና ልጁ ሁለቱም መዝገቡን የማግኘት መብት አላቸው ስለሆነም ወላጁ ወይም ልጁ መረጃውን ይፋ መደረግ ይችላሉ። አንድ ልጅ በወላጅ እውቀት እና ስምምነት የዕፅ አጠቃቀም አገልግሎቶችን ከተቀበለ፣ ይሁን እንጂ ወላጁ ያለ ልጁ ፈቃድ መዝገቦችን ይፋ የማድረግ ወይም የማግኘት መብት የለውም።

## የመዝገብዎን ቅጂ ማግኘት

የሕክምና እቅድ እና ከህክምና መልቀቂያ ማጠቃለያዎ ቅጂዎች ያለምንም ክፍያ እርስዎ ማግኘት ይችላሉ። የ CSB አገልግሎቶችን በሚያገኙበት ጊዜ ወይም ከዚያ በኋላ የመዝገቦችዎን ግልባጭ ለማግኘት በጽሑፍ ጠይቀው ማጠናቀቅ ይችላሉ። እባክዎን የጤና መረጃ አስተዳደር ክፍልን በ 4850 Mark Center Dr., Alexandria, VA 22311 በመሄድ ያግኙ። ከመጨረሻው የአገልግሎት ቀንዎ በኋላ መዝገቦችዎ ለስድስት ዓመታት ያህል ይቀመጣሉ። ለአካለ መጠን ያልደረሱት መዝገቦቻቸው እስከ 24 ዓመት እድሜ እና ቢያንስ ከመጨረሻው የአገልግሎት ቀናቸው በኋላ እስከ ስድስት ዓመት ሊቆዩ ይችላሉ። ሐኪሙ ወይም የሥነ ልቦና ባለሙያው መዝገቦቹን ማየትዎ ለእርስዎ ጎጂ ሊሆን ይችላል ብሎ እስካላመነ ድረስ መዝገቦች ለእርስዎ ይሰጣሉ። ካመኑበት ግን ጉዳት ሊያስከትል ይችላል ትብሎ የታመነበት መረጃ ብቻ ሊታገድ ይችላል። የጤና መረጃ ቅጂዎችዎ የሁለተኛ አስተያየት በመፈለግ ይሁን ወይንም ውሳኔውን ይግባኝ ለማለት በእርስዎ ወጪ የማግኘት መብት አልዎት። ለአካለ መጠን ያልደረሱ ሕፃናት የተመላላሽ ህክምና ይሁን የአእምሮ ጤንነታቸው ወይም የእነሱን የእጽ አጠቃቀም መዝገቦች የማንንም ፈቃድ ሳያሻቸው የማግኘት መብት አላቸው። መዝገቦቻቸውን ለመገምገም የሚጠይቁ ግለሰቦች ጥያቄዎችን መመለስ ከሚችለው አቅራቢ ጋር መዝገቡን እንዲያነቡ ይጠየቃሉ። ለመረጃዎች ግልባጭ አነስተኛ ክፍያ አለ። የግልባጭ ጥያቄ ና የመክፈል ችግር ስልመኖሩ በጽሑፍ ከቀረበ ክፍያው ሊሻሻል ወይም ሊቀነስ ይችላል። መዝገቦችን በቀጥታ ለሌላ አገልግሎት አቅራቢ እንዲተላልፍ ከተፈለገ ምንም ክፍያ የለም።

## መረጃዎችን ማስተካከል መዝገብዎ ውስጥ

በመዝገብዎ ውስጥ ያለን የመረጃ እርማቶችን ሊጠይቁ ይችላሉ፣ ነገር ግን የመጀመሪያው መረጃ አይወገድም። ሰራተኞች በጠየቁት ለውጥ ካልተስማሙ፣ ያልዎትን አቋም የሚያብራራ የራስዎን መግለጫ መጻፍ ይችላሉ። የእርስዎ መግለጫ ከቅጂው ጋር ተያይዞ ይቀመጣል እና በእርስዎ ጥያቄ መሰረት፣ የቅጂውን ግልባጭ ለሚቀበሉ ሰዎች ይሰጣል።

## የቡድን ምስጢራዊነት

ማንም ሰው በቡድን በሚሰጡ አገልግሎት ይሁን የቡድን ማማከር እንዲሁም የክለብ ቤት ያሉ በቡድን አገልግሎቶች ውስጥ የሚሳተፍ ሁሉ ለጋራ ሚስጥራዊነት መስማማት አለባቸው። ይህ ማለት ማንም ሰው ስለሌላው ሰው ምንም እአይነት መረጃ መስጠት ይሁን መወያየት አይችልም ወይም ለሌላ ሰው የአገልግሎቶች ተቀባይ መሆኑን ማሳወቅ አይችሉም።

## የምስጢራዊነት ጥሰቶች

የሚስጥራዊነት መብቶችዎ እንደተጣሱ የሚያምኑ ከሆነ፣ እባክዎን ለአገልግሎት አስተባባሪዎ ይንገሩ ወይም የሰብአዊ መብት ተሟጋችን በ 703.746.3400 ያግኙ። ለበለጠ መረጃ፣ መብትና እና ግዴታ የሚለውን ብሮሹር ይመልከቱ።